የሰ/መ/ቁ. 37575

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ - ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ጠበቃ

**ተጠሪ**፡- ብርሃኑ ልደት ወልዴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሙያ እያገለገሉ ቆይተው የሰራተኛ አበል እና ገንዘብ ሰብሳቢ በመሆናቸው በሕገ ወጥ መንገድ እንደተሰናበቱ ገልፀው ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ሥራዬ ልመለስ ወይም ተገቢው ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ መልሱን ሲሰጥ ተጠሪ እንደሚለው በጥላቻ ውላቸው አልተቋረጠም የተሰናበቱት የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ ነው፡፡ የሚገባቸውን ክፍያ ወስደው ነው የስራ ውላቸው የተቋረጠው የአገልግሎትና የ"2" ወር የማስጠንቀቅያ ወስዷል፡፡ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን የግራ ቀኙን ክርክር ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል በመሆኑም አመልካች ተጠሪ የተሰናበቱት የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ ነው ይበል እንጂ ይህ ለመሆኑ አላስረዱም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በስምምነት የአገልግሎትና የ"2" ወር የማስጠንቀቂያ ተከፍሎት ይገልፃል ይሁን እንጂ የተደረገው ስምምነት በአዋጁ ቁጥር 24 መሰረት በጽሁፍ ለመደረጉ አላስረዱም ሕጉ በሥምምነት የስራ ውሉን ማቋረጥ በጽሁፍ መሆን አለበት ይላል በእርግጥ ተጠሪ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ወስዷል፡፡ የተቀረውን መብታቸውን መተዋቸው በሕግ ፊት ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ውዝፍ ተከፍሎኝ ወደ ስራ ልመለስ ያለውን ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል ምክንያቱም ተጠሪ ውላቸውን በጽሁፍ አላቋረጠም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው የ6 ወር ውዝፍ ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሣቸው ሲል ወሰነ፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የስር ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት አሻሽሎ ተጠሪ በአዋጁ ቁጥር 43/5/ መሰረት የአንድ አመት ደመወዝ ይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2000 ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የተደረገው የሥራ ውል በጽሁፍ አልተቋረጠም ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ እንዳየነው ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ሲሰራ ቆይቶ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ በመቀበል ከሄደ በኂላ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ ካልሆነም ክፍያ እንዲፈፀምለት የጠየቀ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ምንም እንኳ አመልካችም በስምምነት የሚጠበቅብኝን ክፍያ ፈጽሜ አሰናብቸዋለሁ ቢልም የሥራ ውልን በስምምነት ማቋረጥ የሚቻለው በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 25/2/ መሰረት በጽሁፍ የተደረገ ሥምምነት ሲኖር ነው በተያያዘነው ጉዳይ ግን ይህ አልተፈፀመም ስለሆነም ስንብቱ ሕጋዊ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ ከመዝገቡና ከቀረበው አቤቱታ ለመረዳት እንደቻልነው ተጠሪ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ስለመቀበሉ የሥር መዝገብ ይገልፃል፡፡ ይህ ሆኖ እያለ

በሥር ፍ/ቤት ስንብቱን ተከትሎ ተጠሪ ወደ ሥራው ይመለስ ውዝፍ ደሞዝ ይከፈለው ተብሎ ተወስኗል፡፡

ተጠሪ ወደ ሥራው ይመለስ የሚለውን ነጥብ ስናየው ፍ/ቤት በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 43/3/ መሰረት ሰራተኛው ወደ ቀድሞ ስራቸው ቢመለሱ በስራቸው ግንኙነት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር በማጤን ሰራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሚችሉ ሕግ ይደነግጋል ይህ ሆኖ ሳለ ወደ ስራው ተጠሪ ይመለስ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የውዝፍ ደሞዝን አስመልክቶ ተጠሪ ክፍያዎች (የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ) ተከፍሎት እያለ ተጨማሪ ውዝፍ ደሞዝ ይከፈለው መባሉ አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘንም ይሁን እንጂ ተጠሪ ካሣ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ስለዚህ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው ይመለስ መባሉ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23061 በሐምሌ 20 ቀን 1999 እና በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58532 በመጋቢት 22 ቀን 2000 የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ ወደ ስራው ሊመለስም ሆነ ውዝፍ ደሞዝ ሊከፍለው አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ቀደም ሲል የተከፈለው ስለሆነ ያልተከፈለው ካሣ በሕጉ መሰረት ተከፍሎት ይሰናበት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ